# ከሁሉም በላይ ሃብታችን ኢትዮጵያዊነታችን የድህነትና ጠላት አዚምና ደባ መምቻችን አንድነታች !!!

ከተዘራ አስጉ / ከምድረ እንግሊዝ /

## መግቢያ

በመላ ዓለም የምንኖር ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ለሃገራችን አንድነት ፤ ክብር ፡ መልካም ገፅታ ፡ ለሰላሟ ፡ ለኢኮኖሚ ዕድገቷና በአጠቃላይ ያማረች የተከበረች ፤የማትደፈር ፡ በመቻቻልና በመግባባት የሚኖሩባት ምድር እንድትሆን በተለያየ መልኩ በመደራጀት ስንረባረብ ተስተውሏል።

እኛ ኢትዮጵያውያን ከሌሎች ዓለማት ሕዝቦች የሚለየን ለሃገራችን ቀናይ ፡ ብሔርና የተለያየ የመግባቢያ ቋንቋ ባለቤት መሆናችን ጌጣችን እንጂ የሉይነት ዋና ምልክታችን አለመሆኑ በታሪክ የታየ ነው። ሊደፍረን የዳዳን ጠላት ሲያኮበኩብ፡ በምድራችን ችግሮች ሲፈጠሩ የቋንቋና / Dialectal / የብሔር ብሔረሰብ ያልሰፋ ተቀራራቢ ፡ ተዛምዷዊ / Slight related diversity/ ልዩነታችን ዓመት በዓል ስናከብር በጋራ ስንተም እንደምንላበሰው የተለያዩ ለዐይን የሚያማልል የሃገር ልብሳችንና ጌጦቻችን ሲያሻን ተላብሰንና አጥልቀነው የጋራ ሃብታችን አድርገነው የምንጓዘው የጋራ እሴትና የባህል ቅርሳችን እንጂ ጎልቶ የሚታይ የልዩነታችን መገለጫ አለመሆኑ የሚታውቅ ነዉ።

ይህ መልካም በረከት ለረጂም ጊዜ የዳበረ ባሕላዊ ሃብትና ችሮት፡ የምንኮራበትና ያቺ ታላቅዋ እንደምግብ የምትርበን ፤ እንደውሃ የምትጠማን ከአድማስ ባሻገር የምትናፍቀን ሃገራችን ኢትዮጵያ ያላበሰችን በረከተ ካባ በመሆኑ ምንግዜም እምየ ኢትዮጵያ ካደረግችልን፤ ከለገሰችንና ልጆቹ ብላ ከዳር እስከዳር ያለልዩነት አቅፏና እሽሩሩ ብላ ካሳደገችንና ካላበሰችን ክህሎተ ጸጋ አንፃር ሲታይ ለምየ ኢትዮጵያ ልጆችዋ ነፍሳቸውን የሰዉት ይህ ውለታዋና ፍቅሯ እየኮረኮራቸውና እያነሳሳቸው በመሆኑ የውለታው ክፍያ ምላሽ ከብረከተ ልግስናዋ አንፃር ሲገናዘብ ወገን ብዙ ማድረግ እንደሚጠበቅበት የሚያሳይ ነዉ ።፡

ዛሬ ያለነው ትውልዶች ከኢትዮጵያ ሃገራችን ለነፍሳችን የሚያስፍልገን የምናገኘውና የምንምገው ያአማረ አየሯ ፤ ለዐይን የሚያጓጓው የተፈጥሮ ውበቷ ፤ ጥዑም ምግቧ ፤ የተፈጥሮ ሃብቷ፤ በነፃነትና በኩራት በምድሯ መንሸራሸሩና

የመምንሽነሹ ፍላጎቱና  መላ እሷነቷ እየናፈቀን አብረናት ከመኖሩና ከመመኘቱ ባሻገር  ትንሽ ከዝህ በላይ ልናስብ የግድ ይሷል ።

ሃገርና ወገን የሰጡነን አደራ ከልጅነት እስከ ዕውቀት የሃገር ጉዳይ ነውና በተቻለን መልኩ በዉጭ ሃገር የምንገኝ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በግል ፤ በተለያየ ዘርፈ ብዙ ቡድኖችና ፓርቲዎች ፤ ፎረሞችና በግብረሰናይ ድርጂትነት በመደራጀት የተለያዩ እንቅስቃሴዎች በማድረግ ያነገብነው ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ዓላማ ግብ  ይመታ ዘንድ  ሙያዊና ችሎታችን በሚፋቅደው ሁሉ ቃል በገባነው መሰረት ምንም በአካል እናት ምድራችን ብንርቅም መንፋስዋ እየጠራን ፤ ብንለግምባትና አደራዋን ብንበላ የምትታዘበን፤ የሕሊና ወቀሳ ተሸካሚ እንዳንሆን በሚል  ደፋ ቀና የምንለው ለማንምና ለምንም ብለን ሳይሆን ግዴታችን ነው በሚል የግል ተነሳሽነት እንደሆነ የሚታወቅ ነዉ።

ይህ መልካም ስራ ግን በሌላ መልኩና ነገር አለሙ ግራ በገባቸው በአንዳንድ ግለሰቦችና ሰርጎ ገቦች ዘንድ አልዋጥላቸው ካለ" የአቤልና የቃየል" አይነት ክስተት አድርገ ማየት አለብን እንጂ ከያዝነው ዓላማ ቅንጣት ያህል ልናፈገፍግ አይገባም፤፤

ነገር ግን አበው አባቶቻችን " ነገር በምሳሌ ጠላ በብርሌ" ይላሉና እያዋዛው ወደጉዳየ እዶል ዘንድ መነሻ ይሆናል በየ ያሰብኩት ጥንጥን ሃሳብ አጭር ስነ-ፅሁፍ ሆኖ "ወቸው ጉድ" ሳያሰኝ  ወደ አንኳሩ ጉዳዩ ልግባ ።

ለመላው በሃገር ውስጥና በዉጭ ሃገራት ለሚኖረው ወገኖችና በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያን እንዲያስተዳድር አላፊነት ለተሰጠው በብሩህ አስተሳሰብ ይጓዛል ተብሎ ለሚታሰበው የሃገረ ኢትዮጵያ መሪዎች ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ የፖለቲካ ተዋናኞች ፡ ምሁራንና በአጠቃላይ የምየ ኢትዮጵያ ጉዳይ ይመለከተናል ለሚሉ ሁሉ ከሁሉ በፊት ለሃገር ሰላም፤ ጥቅም ፡ መልካም ገፅታና የኢኮኖሚና የልማት ውጥኖች ግብ መምታት ፡ ከግለሰቦች ጀምሮ ሰባአዊ መብቶችን በማስከበር ጉዳይ ፡ድህነትንና ሙስናን በማያዳግም ሁነታ አከርካሪዉን ለመሰበር በመረባረቡ ጉዳይ አፅንዖት ሰጥቶ በመንቀሳቀሱ ጉዳይ ላይ መረባረብ  የግድ ይሷል።

ይህ አጭር ፅሁፍ የትከተበው የተለየ ጉዳይ ለመዳሰስ ሳይሆን ሕዝብ እንደ ሕዝብ የተውሰነ የመንግስታት መዋቅራትና የሹመት ሽርሽር በሚኖርበት ወይም ይኖራል ብሎ በሚያስብበት ጊዜ ባለፈው ወቅት ያልታዩትን ጭብጥ ጉዳዮች በመዳሰስ መልካሞቹ እንዲቀጥሉ ፤ የታዩ ዕፀዖች ካሉና በሚኖረው ክፍተት ጠላት ሽንጉር ብሎ በመግባት ጥቃት እንዳያደርስና የበለጠ ወገን በሃገሩ ጉዳይ ላይ ደጀንና የሚመለከተው መሆኑን ለማስረገጥ ሲባል የቀረበ ፅሁፍ መሆኑ ግንዛቤ ውስጥ ሊገባ ይገባል።

# ኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ ሃገራችን ዳፋና መዳረሻዋ ሰፊና የነገው ትልቅ ደረጃ የመድረስ ህሳቤን አንግበንና እያመቻችን ኢትዮጵያየ አሁን ባለችበት አቀማመጥና የቆዳ ስፋት በአምላክ ክቡር ቃል በሆነው በመጽፍ ቅዱስ፤ በቅዱስ ቁርአን ማንነቷ የተከተበ፡ በታላላቅ ምሁራንና በዓለም ነገስታት ሳይቀር ስሟ የሚወሳ ፡ ታሪኳ የጎላ ፡ የዓለም ምርጥ ከያኒያን ሳይቀር ያዜሙላት የሰው ልጅ መገኛ ፈርጥ / The cradle of human being / የተባለች ፤ ብያቀለጻጽሷትና ቢቀኙላት የሚገባት ታላቅ ሃገር ናት ።

እንዲያው የምየ ኢትዮጵያ ፍቅር  ፀንቶብን ብናወድሳት ፡ ለክብሯ መገለጫ ቃል እያነሰን ብናሸሞነሙናት የሚገባት ሲሆን እንኳን ለልጆቿ ለዓለም ጭቁንና ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ፋና ወጊ ታላቅዋ አምላክ የመረጣት ምድር ናት። ክብር ለአምላክ ይገባዋል የዝች ታላቅ ምድር ፍጡር መሆን ። አንገታችን ቀና አድርገን እንድንተም፡ ኮርታ አኩርታንና የነፃነትን ምንነት አጣጥመን እድንምግ ያደረገችን ሃገረ ኢትዮጵያ እምየ መሆንዋን ለልጆችዋ ግልፅና የማያወላዳ እውነታ ነዉ።

እምየ ኢትዮጵያ ልጆችዋን የማታስከፋ የደግ እናት ተምሳሌት ናት ። እምየ ኢትዮጵያ አስከፋችኝ የሚል እትዮጵያዊ ስለሌለ ክብር ተመስገን። ከደቡብ ፡ ሰሜን ፡ ከምዕራብ ምስራቅ ያሉ ሕዝቦቿን ተከባብሮ ፡ ተፋቅሮ ፡ ተፈቃቅዶ ፡ ተቻችሎ እንዲኖር መስህብ ያላት በሃገር ኮርቶና ተከብሮ መኖርን የሚያጣጥሙባት ዉብ ሃገር ናት ።

ምድረ ኢትዮጵያ ግለሰቦች ፡ ሕዝቦች ፡ ብሄር ብሄረሰቦችና መላ ዜጎች በሰላም እንዲኖሩባት ልቦናዊ መሻት ያላት፡ ኢትዮጵያ የመብትና የነፃነትን ምንነት ብቻ ሳይሆን በዕዉን በነፃነት ፡ በእኩልነትና ከግለሰብ እስከ ማሕብረሰብ የሕዝቦች መብቶች እንዴት ተከብረው መኖር እንደሚቻል ያሳየችና እያሳየች ያለች የነፃነት ተምሳሌት የሰው ልጅ ለመኖር የሚያስፈልጉት ዋና ዋና ተፈጥሮአዊ ንጥረ ነገሮች እንደ አየር ፡ ውሃ  ምግብና መጠጥ  ሁሉ የመብትና የነፃነትን ምንነትና አስፈላጊነት ያበሰረች ህብረ ብሄር ሃገር ናት።

ስለዝህ ከሁሉ በፊት የሁሉም ነገራ ነገር ቁንጮ ሁና ክብር ፡ ታላቅነትና ሞገስ ከፈጣሪ አምላክና ከጎኑ ካሉ ሃያልን ሁሉ ቀጥሎ ልናወድሳትና ልንቀኝላትና ሊቸራት የሚገባ ምድር ብትኖር እምየ ኢትዮጵያ ናት።

# ህዝቦቿ

ሕዝብ ሲባል ከግለሰብ ጀምሮ ማህበረሰብ ከዚያም አልፎ የነዚህ ሁለት ክምችቶ /ስብስቦች/ ማለትም የግለሰብና የማህበረሰብ ውጤት የሆነው የራሱ ወግ ፡ ባህል ፡ ቋንቋ ና የተለያየ መግለጫዎች ያሉት የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦችን ያቀፈ ስብስብና የማህበረሰብ ስብጥር ውጤት ህዝብ ይባላል።

ኢትዮጵያ የአንድ ሕዝብ ውጤት የሆነች ለዘመናት ከትውልድ ትውልድ የተሻገሩ የረዥም ዘመን ተሰባጥሮአዊ አኗኗራዊ ፈሊጥ ያላት ግለሰቦች፤ ማህበረሰቦች ፡ ብሄር ብሄረሰቦች በጋራ ተዋድረው የኖሩባትና የሚኖሩባት ምድር ናት።

# ግለሰቦችና ማህበረሰብ

አንድ ሰው የራሱ ተፈጥሯዊ አካል ይዞና ስያሜ ኑሮት ከሌላው የሚለየው ይራሱ አስተሳሰብ ሊኖረው ወይም የቡድኖችን አመለካከት አጣጥሞና አመዛዝኖ በአንድ ሃገር /በኢትዮጵያ / የሚኖር አንድ ሰው ግለሰብ የሚባል ሲሆን የግለሰቦች/ የሰዎች/ ስብስብ ማህበረሰብ ይባላል።

ማህበረሰብ የተለያዩ ግለሰቦች የራሳቸው አኗኗር ፤አመለካከት፤ግላዊ ፡ መለኮታዊ፡ ሃይማኖት ባህላዊ ዕሴት ወ.ዘ.ተ. እያራመዱ ተቻችለው ፡ ተግባብተው ፡ ለትዳር በቅተው ፡ ተዋልደው የግል ፡ የቡድን ፤የጋራና  ሁሉ አቀፍ ስምምነት ላይ በመድረስ ወይም የሚሻሻለውን እያሻሻሉና እየተወራረሱ የሚኖርበት አብሮ የሚያስጉዝ አብሮ የመኖር መቻት ወይም የመኖር ትብህል ውጤት ማህበረሰብ ይባላል ::

# ብሔር ብሔረሰብ

ብሄር ብሔረሰብ በአንድ አካባቢ/ክልል/ ወይም አካባቢወች /ክልሎች/ በአንድ ሃገር ከሌሎች ሕዝቦች ጋር በመሰባጠር የራሱ ቋንቋ ፡ ባሕል፤ ወግ ፡ ስርዓት ይዞና እያራመደ የሚኖር የመላ ሕዝብ አካል፡ ማህበረሰብ ፡ቡድንና ግለሰቦችንም አቅፎ የያዘ የራሱ ለየት ያለ የኑሮ ትብህል ያለው የአንድ ሃገር ዋነኛ የሕዝብ አካል ነው።

ወደ ኢትዮጵያ ሃገራችን ስንመጣ ብሄር ብሄረሰቦች ባለፉት ዘመናት በአፄዎችም ሆነ በደርግ ስርዓት የነበራቸውን ያአኗኗር ወይም ኢትዮጵያዊነቱን እንዴት ተቀብለው ይኖሩ ነበር የሚለውን በጥቂቱ ምሳሌ መዞ በማውጣት መዳሰሱ የግድ የሚለን ይሆናል ። ከአማራ ብሔር ስንነሳ አማራ ብሔር የተለያዩ ነገዶች ማለትም የታላቁ ነገድ የአገው ፤ የፈላሻ ፡ ከዚያም በጦር እያሸነፈና እየተሸንፈ

የተሰባጠረው የትግሬውና ትግረው ዮኦሮሞው ከዝያም አልፎ ክርስትና በመነሳቱ አኗኗሩ እያአማረ ፡ እየተስተካከለ ፤ አንድ ሕዝብ እየሆነ ፡ የተለያዩ ቋንቋዎችን እየተናገረ፤ እየተጋባና እየተዋለደ ያለውን በአብዛኛው በሰሜኑ ክፍል ከዚያም አልፎ አሁን ወዳአሉት የተለያዮ ክልሎች ማለትም በደቡብ ፡ ቦኦሮምያ ፤ በሐረር ፡ በጋምቤላ ፤ በቤሻንጉል ከዚያም አልፎ እስከ ሱማሊያ ክልል ለኑሮና በጋብቻ ተሰባጥሮ የሚኖረውን አትዮጵያዊ አካል ያካትታል።

ታላላቅ የታሪክ ፀሀፊያን እንደከተቡት በአሁኑ ሰዓት ኑሯቸውን ከትመው እየኖሩ ያሉትን የየአካባቢውን ሕዝቦች፤ ብሔር ብሔረሰቦች ና ግለሰብ ኢትዮጵያዊያንን የኑሮ ተሞክሮና እየኖሩበት ያለውን የጋራ የመኖር ትብዕል ዳሶ መመልከት ስለሚቻል ይህን ግምገማና እውነታ ለባለቤቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለታሪክ ሰወች ትቶ ወደዋናው ቁም ነገር መመለሱ የግድ ይላል።

ከላይ የተጠቀሰው ክስተት አሁን ባሉ በተለያዩ ክልሎች የሚታይ እውነታ ስለሆነ ወንድማማቹ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰብ ወዶት ፡ተቀብሎት፤ ተሰባጥሮ ና እያጣጣመው ያለውን በጋራ ተስማምቶ የመኖር ትብዕል ለየክልሉ ኢትዮጵያዊ መተው የግድ የሚል ሲሆን የአኗኗሩ ዘየ ግን ይበል ፤ እሰየውና ይቀጥል የሚያስብል የኢትዮጵያዊነት አብሮ የመኖር ድባብ እንደሆን ያሰመርበታል።

በቀድሞ ዘመናት ሆነ ፤ በአፄወቹና በደርግ ዘመን የተሻለ ኑሮ ለመኖር፤ ለም የእርሻ መሬት ወዳለበት ፤ ሕዝብ ወደአልሰፈረበት ፡ ሃይማኖትን ለማስፋፋት ፤ በጦርነት አካባባቢውን በማሸነፍና በመሸነፍ በመያዝ የነበረውን ባሕል እንደያዘና የራሱን የሚስጥር ቋንቋ እየፈጠረ እያሻሻለ አሁን ያሉት የቋንቋ / Dialects / ለምሳሌ ቢሉ የአማረኛና የትግረኛ መመሳሰል ፡ የደቡብ ቋንቋዎች ከሰሜኑ ቋንቋወችና የባሕል ተምሳሎቶች ጭብጥና መወራረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታወች እንደሆነና ከአንድ የኢትዮጵያዊ ዘር የተመዘዘ መሆኑን ፀሃፊው ሊያስረግጥ ይወዳል ።

ነገር ግን በተፈጠሩት የመሬት ተሻግሮ መያዝና በጦርነቱ የመሸናነፍ ሰበብ አንዱ ብሔር ሌላውን አሸንፎ በበላይ ለማስተዳደር የተደረገው ጥረት በማንኛውም ዓለም እንደተከሰትው ይህ ክስተት በኢትዮጵያ አልተፈጠረም ለማለት አይቻልም ። ለምሳሌ የኦሮሞው በጎንደርና በሌሎች ሰፊ መሬቶች ያደረገው መስፋፋት ሃይሉን ባያዳክመው ኑሮ የየጁ ኦሮሞ በሰሜኑ ክፍል ያለው ሃይልና የሕዝብ አሰፋፈር አሁን በስልትና አብሮ በመኖር መላ በብዙው የኢትዮጵያ ክፍል ውስጥ ተባዝቶ እንደሚገኘው የአማራ ሕዝብ ኦሮሞውም ተመሳሳይ ያአኗኗርና በየቦታውና በየክልሎች ሰፍሮ የመገኘት ሁኔታ ይፈጠር እንደነበር ታሪክ ያሳየናል።

ይህም ሁኔታ በየቦታው በንግድ ፡ ከቦታ ቦታ መዘዋወርና በጦርነት ተሸናንፎ በየክልሉ የቀረው ብሄር ብሔረሰብ ሕዝብ አትዮጵያዊ ወንድምነቱን ፡

እህታማችነቱንና ከአንድ ዘር ግንድ የተሳበና የወጣ ሕዝብ መሆኑን የሚያመላክት እሰየው የሚያሰኝ የኢትዮጵያዊነት ድባብ ነው።

ሌላው በጦርነት መሸናነፍ፣ በጉልበትና በጠር መሳርያ ብዛት የሙብት መነጣጠቅና አንዱ ብሄር ሌላውን መስሎ እንዲኖር የማስገደዱ ሁኔታ ቢታይም ይህ ክስተት በሌሎችም የዓለም ክፍሎች ተከሰቷል ። ይህም የሆነው የኢኮኖሚ የበላይነት ለመያዝና ተሻግሮ የሄደው ሕዝብ በእግሩ ፀንቶ የመኖር ፍላጎትና በየሔዱበትና ባቀኑት ወንድማዊ መሬት መፈናቀል እንዳይኖር በማሰብ እንጂ ያን ያህል የመጨቋቆንና ሆን ብሎ ሙብት የመጋፋት አካሄድ ነበር ለማለት የማይቻል ሲሆን ምድሩና መሬቱ የኢትዮጵያውያን የጋራቸው መሆኑ ተረስቶ እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል።

ስለዝህ በቀደምት ጊዜ የነበረው ስብህናን ፤ሙብትን አስከብሮና አክብሮና ቅድምያ ሰጥቶ ከብሐር ብሔር ሰብ አባላትና አትዮጵያውያን ሕዝቦች ጋር አብሮ የመኖር፤ በጋብቻ የመተሳሰሩን ፤ አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ ተባብሎ ፤ ተግባብቶ ፤ ተቻችሎና ተፋቅሮ በቋንቋ ሳይለያዩ፤ ከየት መጣሽ ከየት መጣህ ፤ የማን ብሔር ነህ የማን ዘር ሳይባባሉና ልዩነቱን ሳይለጥጡ በኢትዮጵያዊነት የመኖሩ ትብህል በአሁኑ ጊዜ ካለው ስርዓት ማለትም አንድነት በልዮነት አብሮ በመቻቻል መኖር /Unity in Diversity / ከሚለው የጊዜው በጋር የመኖር ስልት እየተዛመደ ቢሄድ መልካም ኢትዮጵያ ትፈጠራለች ተብሎ በብዙ ኢትዮጵያዊያን የሚነሳና በመሆኑና እየሆነም ስለሆነ ይህ ዕምርታ ሊገፋበትና ያለው መንግስታዊ ስርዓትም ይህን አካሄድ ለዛሬዋና ለነገዋ አትዮጵያ አብሮ የመኖር ትብህል ወሳኝ አካሄድ መሆኑ ግንዛቤ ውስጥ ሊያስገባ ይገባል።

## መልዕክተ ማጠቃለያ

ኢትዮጵያዊነትን ከሁሉ በፊት ማስቀደም በመላ ኢትዮጵያውያን ልብ የተከተበ ፣ በማንም በምንም የማይለወጥና በደማችን ስር የሚዘዋወር የኢትዮጵያውያን የልብ አውታር ማንቀሳቀሻ ሞተርና ጥንስስ መሆኑ ግልፅና የማያወላዳ እውነታ ነው ። መከባበር ፣መቻቻል ፤በፍቅር መኖርና ኢትዮጵያዊነታችን ሲነካ ፣ ሊደፈር ሲሞከር፤ እምየ ኢትዮጵያ በክፉ ስትነሳና ጠላት ስያኮበኩብ ከዳር ጋምቤል ፣ቤንሻጉል፤ ከትግራይ ፣ አማራ ፣ኦሮሞ ፣አፋር ፣ ሶማሌ፣ ሐረር ሌላው ብሔር ብሔረሰብ በሙሉ ማንም ቀስቃሽ ሳይኖረው በጥቅሻ ብቻ እንደንብ ለደንበሩ ፣ለአንድነቱ ፤ለክብሩና ለማንነቱ ሆ ብሎ ልዩነቱን ወደ ዳር አርጎ የሚነሳ ሕዝብ መሆኑን ሊጤን ይገባል ።

ይህ ትዕብላችንና ለዘምናት ያፈራነው የኢትዮጵያዊ ማንንነት መግለጫችን አልዋጥላቸው ያሉ ያአምና ወንድም ተብየዎች እንደሻብያና አልሻባብ ያሉ ዓይናቸው በቅናት የተንፈረፈረና የነዚህን ጉርሻ የለመዱ የእናት ጡት ነካሾች ይህን ቱፊታችንን ሊያተረማምሱ አንድ ቋንቋ እየተናገሩ ፣ አንድ አይነት ምግብ

እየበሉ ፡ በመልካችንና በማንነታችን ተምሳስለው፤ የውሸት ጃኖ በመላበስ እያደቡና በእየ መስሪያ ቤቱ ብቅ ጥልቅ እያሉ ሊያደንቅፉና ጊዜ በመጠበቅ እያደቡ ቢሆንም "ምሬ ላልምርህ  የቲዎድሮስ ፡ የዮሃንስ ፡ የሚኒሊክ ፤የአሉላ ፡የጦና፤ የአሊ ሚራ ፡ ያአባ ጅፋር ፤ ያባገዳ ፤ያየሎምና የሌሎች ጀግኖች ግርፍ ውጤቶች ነንና " ዋ ! ዋ ! ዋ ! ልንላቸው ይገባል ።

ትላንት በኢትዮጵያ ዋና ዋና ከተሞች በወንድማዊ ኢትዮጵያዊነት ሲኖሩ የነበሩ የሻብያ አቀንቃኞችና ቡችሎች እንድሁም ኢትዮጵያዊነት በቃን ብለው በሪፈረንደም አረጋግጠውና ድምፅ ከሰጡ በኋላ የኢትዮጵያ መንግስት ትዕግስቱ በዝቶ በየመስሪያ ቤቶች፡ በየሚኒስተር ቢሮወች የሃላፊነት ስራ ይዘውና በየኢምባሲዎች ተሸጉጠው በማናለብኝነት የኢትዮጵያውያንን  አፍ ሊሸብቡና የየብና ቤቱቾ ጀግና ሁነው "ከኛ በላይ ላሳር" በማለት  ኢትዮጵያዊያንን "ወቸው ጉድ እስኪ የኢትዮጵያ አምላክ ያውቃል" በማለት በትዕግስት አልፈናቸው እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነዉ።

ከዝያም አልፎ በአጎራባች ደንበራችን ትግራይ ፤ ጎንደር ፤ ወሎና መሰል ደንበር የኢትዮጵያን እህሎች ዋና አከፋፋይ በመሆን የዋሁን ገበሬ በተሳሳተ ገንዘብ /Forged money/ እህል እየጉዙና ከዝያም አልፎ የድፍረታቸው ድፍረት ኢትዮጵያዊውን ቡና በኤርትራ የተሰራ ብለው ሲያከፋፍሉና የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ያለ ኤርትራ ፍቃድ ወይ ፍክች ብለው የኢትዮጵያዊያንን ቀሽት አሳረው እንደነበር የአደባባይ ሚስጥር ነው።

በየኢምባሲው ተሸጉጠው የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፈው ከመስጠት ባሻገር ቱሪስቶችና ጎብኝወች ለቪዛ በየኢምባሲው ሲመጡ በኤርትራ ኢምባሲወች በኩል እንድያልፉና ታላላቀች ቅርሶቻችን እንደ አክሱም፤ ላሊበላና ፋሲለደስ የኤርትራ አካል እንደሆኑ በራሪ ፅሁፎችን ፤ ፍላየሮችንና የጉዞ መረጃወችን በማዘጋጀት የኤርትራን የገቢ ምንጭ እንድታገኝ የማድረግ ሴራ ያጧጧፉ እንደነበር በኢንግሊዝ ሃገር ያሉ ጎብኝ ወዳጆቻችን ያካፈሉን ያምና ሚስጥር እደሆነ መረጃውን ጃባ ልንል የግድ ይላል ።

ከዝያም እነዚህን የንግድ አሻጥሮች አቁሙ ሲባል በሃገራችን የኤርትራ ደንበሮች ባድሜ የኛ ናት በሚል የቁራ ጩህት በማስተጋባት ከሃጎራባች የረጂም ጊዜ ጠላቶቻችን ሃገሮች ጋር ተባብረው ጦርነት ቢጭሩም በጀግናዎቹ የኢትዮጵያ ብሔር ብሄርሰቦች ልጆች የጋር ምከታና አይቀጡ ቅጣት ተመትተው "ዳግሚያ አደዋ "በምድራችን በአዲሱ ትውልድ ተከትቦ ድባቅ ተመተዋል፤፤

ዛሬ ዛሬ ደግሞ በውጣ ውረድ ኢትዮጵያዊው የሚያገኘውን ቢጫ ካርድ / Yellow ID card  / ዳጎስ ያለ ገንዘብ በመክፈል የኢትዮጵያ ተወላጂነት መታወቅያ ካርድ ይዘው የሚንቀሳቀሱና አንጀታችንን እያቆሰሉንና ሚስጥርም እያቃረሙ ለሻብያ በማስተላለፍ፤ ወደ ሃገር ቤት እየተሻገሩና በየቆሰላው ፅ/ቤት ተወሽቀው እንዳሉና የባድሜ ሽንፈት ቁጭታቸውን እንደለመዱት በቢሮ አሻጥርና

ሙስናን በማስፋፋት ታላቅ ሃገር የማጥፋት ስራ ለመስራትና በየውጭ ሃገር የዲያስፖራ የኮሚኒቲ ተወካዮች ሆነውና ለመሆን ከእናት ጡት ነካሽ ኢትዮጵያውያን ጋር በተለያየ ጥቅማ ጥቅም በደርግ ጊዜ ያከናውኑት የነበረውን አሻጥር ለመፈፀም ሽርጉድ በማለት እንደትላንቱ ሃገረ ኢትዮጵያን ሊያምሱ ደፋ ቀና ከማለት አንዳልቦዘኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

እንዳለፉት አፄዎች የኤርትራውያን አፈጋጬችና ባንዳዎችን በጋብቻ እያስተሳሰሩና እያማለሉ እንዲሁም እንደደርጎቹ የጭንን ማሃል አገዳ እየኮምኮሙና ገንዘብን እያፈሰሱ እንዲሁም በጦርነት አረንቋ እየተማገዱ በግድ ከራቀዋት እናታቸው ለማቀራኘት ማሰቡ በረጂሙ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ተሞክሮ የታየ በመሆኑ አካሔድ ሊፈተሽ የሚጋባ ይሆናል ። ኤርትራዊያን ወደው የገብቡተን ከኢትዮጵያ ጋር ተልይቶ የመኖር ፍላጎት የራሳቸው ብቻ ምርጫ መሆኑ ግልፅ ሊሆን ይገባል ።

ከዝህ ባሻገር ከኤርትራ መሪያቸውና ከአስተዳዳሩ ማንቆና ረገጣ ለማውጣት የሚደረግ ዉጣ ዉረድና ጣልቃ ገብነት ካለ ይህ የኤርትራውያን ምርጫና አለአማቀፋዊ መተጋገዝ ቢኖርም አሁን አገራችን እያራመደችው ያለውን የኢኮኖሚ ሂደትና ክንውን የሚያንጋና ከጎረቤት ሃገሮች አብሮ በሳላም የመኖር ሂደት ህግጋት ባተገናዘበ መልኩ መሆን አለበት።

"ያለበት ይበንበት" እንዲሉ ትንሽ የደም ጠብታ ዝምድና ያላቸውን ወገኖችና ባለስልጣኖች ለማስደሰት ተብሎ የሚደረግ የሽፍጥ ስራ ካለ የኢትዮጵያውያን ሃብት የሚያወድምና ብሎም መልካም አመለካከት ባለመሆኑ በቃ ሊባልና መስመር የለቀቀው አካሄድ መላ ሊባልለት ይገባል።

ከዝህ ሌላ በአጎራባች የአማራና የትግራይ ክልል ሁመራ ፤መተማና በተለያዮ አዋሳኝ ከተሞቻችን ደምበር እየዘለሉ በመግባት ሕዝብን የማወክና የጠለፋም የውብድና ስራ በምስራት ወገንን በኤርትራ ክርሺሌወች ቁም ስቅል እያሳዩና በባድሜ ጦርነት የጀብድ ስራ ሲሰሩ የተማረኩ ወገኖቻችን ሁኔታ እየከነከነን ባለበት ወቅት እንዲህ ያለው የማን አለብኝነት ድርጊታቸው በእርምሞ መታየቱ የሚያሳዝን ነው። በኤርትራ ክርሽሌ የሚማቀቁ የኛ ወገኖች ሳይፈቱ የነሱ ምርኮኞች ያለልዋጭ እንዲፈቱ ማድረጉ ትንሽ ስለሚከነክን መላ የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት በጉዳዮ ላይ አፅንኦት ሰጥቶ እንዲንቀሳቀስ ወገንን እያሳሰበ መሆኑ የሚታወቅ ነው ።

በስደተኝንት ኢትዮጵያ ሃገራችን ዉስጥ ያሉ ኤርትራዊያን በዓለም አቀፉ የስደትኝነት ሕግጋት እንዲስተናገዱ የማድረጉ ሁኔታ ሊታሰብበት የሚገባና የተለያዩ የትምህርት ሆነ ወደ ቤተሰቦቻቸው ወደ ዉጭ ሃገር ሲቀላቀሉ ከመርጃ ማካፈል ሁኔታውች በራቀ መልኩ አካኤዶች ተስተካክለው ቢሰሩ መልካም ሲሆን የኛ ነገር " ለኢትዮጵያ የደግነት ስራ ከፋይዋ ታላቁ አምላክ ቢሆንም " ይህ ሁሉ ውለታ እየተደረገላቸው እንኳን አገራችንን በመጥፎና በክፉ ከማንሳትና

የአደራ ወጭት ሰባሪ ረጂም ምላሳቸው ሲጎለጎል ላየ በአሜሪካ ፤ካናዳና አውሮፓ ለምንኖር ኢትዮጵያዊያን እያስደመመንና እያስገረመን ይገኛል።

ኢትዮጵያ ሃገራችን ላከበሩ ፤ ሰላሟን ለተምኙ ፤ በማንነቷና በዕልውናዋ ካልመጡ አምጣ በወልደቻቸውና ባሰደገቻቸው ልጆቿ ካልመጡባት እጇ ሰፊ ፡ "ሁሉ በጄ ሁሉ በደጄ ግቡና ተቋደሱ" የምትል የቀኖች ፡ የደጎችና የአርቆ አስተዋዮች ሃገር ናት ። ካስቆጥዋት፤ ሊደፍሯት ለሞከሩና የበሉበትን ወጭቷን ሊሰብሩ ለዳዱ ግን የእግር እሳት መሆኗ ሳይታልም የተፈታ እውነታና በትሞክሮም የታየ ነው።

ትእግስት ፡ አይቶ እንዳላዩ ማለፍ የአዋቂነትና ከአበው አባቶቻችን የአፈራነው ቅሪት ሃብት መሆኑን በዳግሚያዋ አድዋ በባዲሜ ወረራና የጦር ሜዳ ውሎ የታየ በመሆኑ "ነገረው ነገረው ኋላ ግን መከራ ይምከረው " እንዲሉ ያለፋትን ታሪኮች መለስ ብሎ አንብቦና አጥንቶ ከውዲሁ ከድፍረትና ከአጉራ ዘለልነት መታቀብ የግድ ይሏል።

የኢትዮጵያ ብሔርብሄረሰቦች እንደጥንታቸውና እንዳምናው ተዋልደው፤ ተጋብተው ፡ አንዱ ህዝብ ከሌላው ምድር በወንድምነት እሽት ቆርጦ የሚቃመስበትና አብሮ የመኖሩን ትብዕል አዳብሮ በጋራ አርሶ፤ ጎልጉሎ፤ ሰርቶና መከሩን ሰብስቦ በወል ሃገሩ ኢትዮጵያ ይኖራል እየኖረም በመሆኑ የኢትዮጵያ አምላክ ክብር ምስጋና ይግባው ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም በሕዝቦችዋ አንድነት ተክብራ ትኖራለች ።

ፍሬዋ ፤ መከሯ ፤ ዕምቅ ሃብቷና የጋራ መገለጫ ባሕሏ የሕዝቦቿ የጋራ መገለጫዎች እንደሆኑ ለዘላለም ይኖራል ።

የድህነት መጋረጃና ደንቀራ በሰላም አብሮ የመኖር በረከተ ፀጋ መቀመቅ ይገባል ።

ተዘራ አሰጉ
ከምድረ እንግሊዝ